# ከበረከት አቤቱታ የገረሙኝ ነገሮች!

ትናንትና አቶ በረከት የጋዜጠኝነትን ሀሁ ከማያውቀው ዶማ የመዝናኛ ዝግጅት አዘጋጅ ፌዘኛ ሰይፉ ፋንታሁን ጋር ያደረገውን ቃለምልልስ ከዩቲዩብ (ከፈለገ እናንት) ማጎደር ሐምሳ ምናምን ብር ፈጅቾ አዳመጥኩት፡፡

ቆይ ግን እናንተ ቴሌ ዋጋ ቀንሻለሁ አላለም ነበረ??? ነው ወይስ ገና ተግባራዊ አልተደረገም??? ወይስ እኔን አይመለከትም??? ቴሌ በእኔ ላይ የተለየ የአገልግሎት ቀረጥ እንዳለው ለምጠቀመው ፌስቡክ (መጽሐፈ ገጽ) በቀን ከሐምሳ ብር በላይ ሲላጨኝ እንደከረመ ስነግራቹህ በከፍተኛ ቅሬታ ነው፡፡ እንዳልተወው እንዴት ብየ??? እንዳልቀጥልበት በጣም ከአቅሜ በላይና ጣራ የነካ ሆነብኝ!!! አልብላ አልጠጣ ብየ ነው በማኅበራዊው የብዙኃን መገናኛ ንቁ ተሳታፊ ሆኘ የምታዩኝ ኖሮኝ አይደለም፡፡

እንዴት ሆኖ ነው ታዲያ ቴሌ እንዳለው ይሄ ታሪፍ (የአገልግሎት ቀረጥ) በዓለም አቀፍ የታሪፍ አጣጣል ደረጃ መሠረት ከሕዝቡ አማካኝ ገቢ ከአምስት በመቶ እንዳያልፍ ተደርጓል ሊለን የሚችለው??? ቴሌ መልስ ይስጥበት!!! የሕዝቡ አማካኝ ገቢ ስንት ሆኖ፣ አንድ ሰው በቀን ምን ያህል ሰዓት የኢንተርኔት (የዐውደ መረብ) አገልግሎት የመጠቀም መብት ወረም ደረጃ አለው ተብሎ ታስቦ ነው አሁን ያለው ታሪፍ ሥራ ላይ የዋለው??? ቴሌ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበትን አሠራር እከተላለሁ ካለ ይሄንን ጥያቄ አጥርቶ ለሕዝብ ይመልስ???

ወደ ጉዳያችን እንመለስና ሰይፉ ፋንታሁን እራሱን እንደጋዜጠኛ የሚቆጥር ከሆነ ይሄንን ቃለ ምልልስ ከማቅረቡ በፊት በረከት ከሚከሳቸው ወገኖች ምላሽ በማካተት ሚዛናዊነትን መጠበቅ ነበረበት፡፡ በተጨማሪም ከሚያውቀው እውነታ በመነሣት በረከትን መሞገት ነበረበት፡፡ እሱ ግን ይሄንን አላደረገም፡፡ በረከት መርዙን ረጭቶ እንዲሔድ ብቻ ነው ያመቻቸለት፡፡ እውነት የብሮድካስት (የሥርጭት) ባለሥልጣን የተለወጠ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሚሰማው ከሆነ በሕጉ መሠረት በሰይፉ ፋንታሁን ላይ እርምጃ ወስዶ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ እናውቃለን ሰይፉ ማለት የወያኔ ሎሌ እንደሆነ፡፡ የጋዜጠኝነት ትምህርት ሳይኖረው የጋዜጠኝነት ፈቃድ አግኝቶ እንዲሠራ ያደረገው ወያኔ ስለሆነ አገዛዙን በታማኝነት ነው ማገልገል የሚፈልገው፡፡

ከበረከት አቤቱታ የገረሙኝ ነገሮች፡-

* "ወላጆቸ ከኤርትራ የመጡ ቢሆኑም አማራ ክልል ተወልጀ አፌን በአማርኛ የፈታሁ በመሆኔ አማራ ነኝ! ማለቱ፡፡

ይገርማል! አመናቹህም አላመናቹህ በኢትዮጵያ የዜጎች የብሔረሰብ ወይም የጎሳ ማንነት ብየና በዘር ሳይሆን "አፍ በሚፈታበት ቋንቋ ነው!" ብሎ ለመናገር አቶ በረከት የመጀመሪያው ሰው ናቸው፡፡ አገዛዙ ሲሠራበት የኖረበት የዜጎች የብሔረሰብ ወይም የጎሳ ማንነት ብየናም ዘርና የዘር ቋንቋ እንጅ አፍ የሚፈታበት ቋንቋ ሆኖ አያውቅም፡፡ በእርግጠኝነት በረከት እንዲህ ዓይነቱ አሠራር አለ ለማለት የሚጠቅሰው አንድም የሕገመንግሥታቸው ወይም የአዋጃቸው አንቀጽ የለም፡፡ ስለሆነም በረከት በዚህ አነጋገሩ ተራ አወናባጅና ውሸታም መሆኑን ነው ያረጋገጠው፡፡

እንዲህ ቢሆንማ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎ፣ ሸዋ ያሉ አፋቸውን በአማርኛ የፈቱ የትግሬ ወይም የሌላ ጎሳና ብሔረሰብ ልጆች በብሔራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ላይ አማራ ተብለው አንመዘግባቸውም ነበር እንዴ ታዲያ??? የአማራ ክልል በሚሉት ብቻ ሳይሆን በተቀረው የሀገሪቱ ክፍል ባሉ ከተሞች ለምሳሌ በአዲስ አበባ፣ በናዝሬት በደብረዘይት፣ በአዋሳ፣ በሀረር፣ በድሬዳዋ ወዘተረፈ. ከተሞች በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ የሌላ ጎሳና ብሔረሰብ ልጆችንም ጭምር ማለቴ ነው፡፡ እናም የአቶ በረከት አማራ ሳይሆን የአማራ ክልል ባለሥልጣን መሆን ስለማይችል ከገጠመው ወጥመድ ለማምለጥ ሲጨንቀው የተናገረው ተራ አነጋገር ነው እንጅ እንዲህ ዓይነት አሠራር ኢትዮጵያ ውስጥ ኖሮ አያውቅም፡፡

* መጽሐፍ ለማሳተም የሚበቃ አቅም የለኝም ብሎ መጽሐፉን "በደጋፊዎች (በስፖንሰር) ነው ያሳተምኩት!" ማለቱ፡፡

በረከት በሙስና በርካታ ሀብት ካካበቱ የወያኔ ባለሥልጣናት አንዱ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ታዲያ እንዴት ሳያፍር እንዲህ ሊል ቻለ? ብለን እንጠይቅ ይሆናል፡፡ ይመስለኛል በረከት ሥልጣኑን በመጠቀም ገንዘብ የተቀበላቸው ባለሀብቶችና ይሄንንም የሚያውቁ የክልልና የማዕከላዊ መንግሥት የሚባሏቸው ባለሥልጣናት ለየራሳቸው ጥቅምና ደኅንነት ሲሉ ባለሀብቱ ወንጀለኛ እንዳይባል "ከኔ ይሄንን ያህል ገንዘብ በሙስና ወስዷል!" በማለት፣ ባለሥልጣናትም የተነካኩ ስለሆኑ "ይሄንን ያህል ገንዘብ ከእከሌ ባለሀብት በሙስና መቀበሉን አውቃለሁ!" በማለት ይሄንን ምሥጢር ሊያወጡ እንደማይችሉ በመተማመን ነው ድርቅ ብሎ ዓይኑን በጨው አጥቦ በባሕርዳርና በአዲስአበባ ስንት ድርጅት በግሉ እና ከባለሀብቶች ጋርም በድርሻ እያለው፣ በውጭ ሀገራት ባንኮችም (ቤተንዋዮችም) በበርካታ ቢሊዮኖች (ብልፎች) የሚቆጠር ዶላር እንዳለው መረጃዎች እያረጋገጡ ምናምኒት የሌለው ድሃ እንደሆነ አድርጎ ለመናገር የደፈረው፡፡

* የአማራን ሕዝብ "ጨቋኝ ትምክህተኛ!" እያለ ሲያሳቅቅ፣ ሲያሸማቅቅ፣ አካላዊና ሥነልቡናዊ ጥቃት ሲያደርስ መኖሩ እየታወቀ አሁን ድንገት የአማራን ሕዝብ አክባሪ ሆነና "በታሪኩ ሰው አፈናቅሎ የማያውቅ ደግ አስተዋይና ትልቅ ሕዝብ አሁን ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ሰዎችን ማፈናቀል የጀመረው!" ብሎ የአማራን ሕዝብ በአፈናቃይነት በመክሰስ ይሄ በመራራ ብሶት የተፈጠረው የአማራ ብሔርተኝነት እንዳይፈጠር እንደሱ ሐሳብ ብአዴን የሚፈጅውን ፈጅቶ ይሄንን የአማራ ብሔርተኝነትን መደምሰስ፣ ማክሰም፣ ማጥፋት ሲኖርበት ብአዴን ከአቅሙ በላይ በመሆኑ ሳያደርገው መቅረቱ ከንክኖት ነው ለአማራ ብሔርተኝነት እዚህ መድረስ የብአዴን ባለሥልጣናትን ተጠያቂ ማድረጉ፡፡

በረከት እዚህ ላይ በግልጽ ነው ፀረ አማራ አመለካከቱን ያንጸባረቀው፡፡ ወያኔ የአማራ ክልል ብሎ የከለለውን የአማራን መሬት በዙሪያው ላሉ አሳልፎ በሰጠው ኢፍትሐዊ አከላለል ምክንያት የአማራ ሕዝብ ጥያቄ ያነሣባቸውን አጎራባች ክልል ተብየዎችንና ሱዳንንም ሳይቀር እየጠቀሰ የብአዴን ባለሥልጣናትን ".... በማለት ሕዝቡን እየቀሰቀሱ ነው ቀውስ እንዲፈጠር ያየረጉት!" በማለት ከሷል፡፡

የበረከት ፍላጎት አማራ የተወሰዱበት መሬቶች እንደተወሰዱ እንዲቀሩ ነው፡፡ አማራ እነኝህን መሬቶች መጠየቁ አንገብግቦታል፡፡ ይባስ ብሎም እንዲያውም የአማራ ሕዝብን ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለማጋጨት በማሰብ "ሕዝቡን እየቀሰቀሱ ነው!" የሚላቸውን የብአዴን ባለሥልጣናትን እርግጠኛ ሆኖ "ወደፊት ኢትዮጵያን ችግር ላይ የሚጥሏት እነሱ ናቸው!" በማለት ተናግሯል፡፡ እንደ በረከት ዕይታ አማራ ጥቅሙንና መብቱን ማስከበሩ ኢትዮጵያን ችግር ላይ መጣል ነው፡፡ ኢትዮጵያ ችግር ላይ እንዳትወድቅ የአማራ ሕዝብ ጥቅሙን ማጣት፣ መብቱ መረገጥ አለበት፡፡ አይገርምም???

ሌላው በረከት ለአቶ ገዱ አንዳርጋቸው ይሄንን አቅርቤለት ነበረ፣ ለአቶ ደመቀ መኮንን እንዲህ ብየው ነበረ ያለው ነገር ግን ውሸት አይመስለኝም፡፡ ዓላማው ግን እሱ እንዳለው ያንን ያደረገበት ምክንያት ሕዝብን ተጠቃሚ ለማድረግ አይደለም፡፡

እዚህ ላይ ስለአቶ በረከት ስናስብ አንድ መታወቅ ያለበት ነገር አለ፡፡ የትም ቦታ ብትሔዱ የአቶ በረከት አቀራረብ (approach) በሥርዓቱ ደስተኛ ያልሆነ፣ የሚቃወመው ብዙ ነገር ያለ መስሎ አገዛዙን እያማ፣ ከድሮ ጀምሮ ለመልቀቅ እንደሚፈልግ በማውራት ነው ሰውን የሚቀርበው፡፡

አብረውት የሠሩትን ሰዎች ብትጠይቋቸው ይሄንን ያረጋግጡላቹሃል፡፡ በትክክለኛ ገጽታ ግን በረከት በአገዛዙ ውስጥ ቁጥር አንድ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰው ነው፡፡ መለስን ሳይቀር መጠምዘዝ የሚችል ሰው ነው፡፡

በረከት በእንዲህ ዓይነት አቀራረብ አብረውት የሚሠሩትን ከሕወሓት ውጭ ያሉ ሰዎችን የሚቀርብበት ምክንያት ለመሰለል እንዲመቸው ስለወያኔ ምን እንደሚያስቡ በልባቸው ያለውን አውጥተው እንዲናገሩ ለማግባባት በማሰብ ነው፡፡

በረከት ለሕዝብ አሳቢ ተቆርቋሪ መስሎ ወያኔን እያማ እየተቸ የሚቀርብበት ምክንያት የጤና እንዳልሆነ ወይም ለተንኮል እንደሆነ የሚታወቀው ወያኔን እያማ ሲቀርባቸው እውነት እየመሰላቸው ጨምረው ያሙለት ሰዎችን አዘናግቶ ሌላ ምክንያት ተፈልጎላቸው ሲሙቱ ሲታይ ነው፡፡

እናም በረከት የለውጥ ሐሳቦችን ቀድሜ ያቀረብኩት እኔ ነኝ፣ ለገዱ እንዲህ አድርግ ብየው ነበረ፣ ለደመቀ እንዲህ ብየው ነበረ ያላቸው ነገሮች ሐሰት አይመስሉኝም፡፡ ዓላማቸው ግን ከላይ እንደገለጽኩት ለስለላ "እስኪ ምን ያስባሉ?" የሚለውን ለመገምገም ለማወቅና ቀድሞ እርምጃ ለመውሰድ በማሰብ እንጅ ፈጽሞ በጎ በማሰብ አይደለም፡፡

እናም የአቶ በረከት እባብነት በቃላት ለመግለጥ የሚቻል አይደለም፡፡ ራሱን ሰይጣንን ቁጭ አድርጎ ተንኮል ሸፍጥ ሴራ ማስተማር ማሰልጠን የሚችል እጅግ ሲበዛ ሸፍጠኛ፣ ሴረኛ፣ አሻጥረኛ ነው፡፡ እናም ይሄ የሚባለው የለውጥ እንቅስቃሴ እውነት ከሆነ ይሄ ሰው በቁጥጥር ስር ውሎ በፈጸመው ዝርፊያና ግፍ ልክ ፍርዱን እንዲያገኝ ካልተደረገ በስተቀር ለማየት ያብቃቹህ ሀገሪቱን ግልብጥብጧን ያወጣታል፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com